# <u>LE  DICTATEUR</u>

## ***<u>አምባ  ገነን</u>***

*(አሥራደው  ከፈረንሳይ)*






Un dictateur n'est qu'une fiction. Son pouvoir se dissémine en réalité entre de nombreux sous - dictateurs anonymes et irresponsables dont la tyrannie et la corruption deviennent bientôt insupportable.

(G. LE BON- « Hier et demain »)

***አንድ አምባገነን ውሸታም ፍጡር ነው፤ እንደ እውነቱ ስልጣኑም የተመሰረተው የእሱ አምሳያ በሆኑ ብዙ ያልታወቁ ጥቃቅን አምባገነኖችና ሃላፊነት በጎደላቸው ሆድ አደር ፍጡሮች ትብብር በመሆኑ፤  የስልጣን ብልግናው፤ ጭቆናውና ንቅዘቱን (ሙስናውን) መሸከም ለሕዝብ ከአቅሙ በላይ ይሆናል ።***

***(ጂ ለ ቦን - «የር ኤ ደመን፤  ትናትና እና ነገ »)***

Tous les efforts de la violence ne peuvent affaiblie la vérité et ne servent qu'à la relever davantage. Toutes les lumières de la vérité ne peuvent rien pour arrêter la violence et ne font que l'irriter encore plus.

(Blaise PASCAL – « Les provinciales »)

***ዕውነትን ለማፈን የሚደረግ ማንኛውም የሃይል እርምጃ፤ ዕውነትን ከማዳከም ይልቅ፤ ሃይልና ብርታት እየሰጣት ይበልጥ እንድትለመልምና እንድታብብ ያደርጋታል ። ዕውነት የምትፈነጥቀው ብርሃን የጨቋኞችን ግፍ አጉልቶ ከማሳየቱም በላይ በመጋለጣቸው ይበልጥ እንዲሰጉና እንዲጨነቁ ያደርጋቸዋል ።***

***(ብሌዝ ፓስካል « ለ ፕሮቨንሲያል »)***

Exterminez, grands dieux, de la terre où nous sommes, Quiconque avec plaisir répand le sang des hommes !!

VOLTAIRE – « Le fanatisme »

*ያለንባት ዓለም ፈጣሪ የሆንከው ትልቁ አምላክ ሆይ፤ የሰውን ልጅ ደም በማፍሰስ የሚደሰተውን ማንኛውም ጨካኝና እኩይ ፍጡር ከዚህ ዓለም አሰወግደው !!*

*(ቮልቴር « ለ ፋናቲዝም »)*

- *ነፃነት የዕምነት ጉዳይ ነው፤ በራሱ የሚተማመን ትውልድ ነፃ አገር አስረክቦን አልፏል ። በራሱ ዕምነት የጎደለው ትውልድ ደግሞ ነፃነቱንና አገሩን ለባዕድ አስረክቦ፤ ክብሩን አዋርዶና፤ የበታች ሆኖ በረሃብ ይሞታል !*

- *እንደ ውሻ ሳይሆን እንደ ሰው ሆኖ መሞት ለሰው ልጅ ከፈጣሪ የተሰጠው መብት በመሆኑ ውሻ ሳይሆን ሰው ሆነል ለመሞት እንጣር !*

- *ያጣነውን ሕይወት እንደገና ለመኖር ከፈለግን፤ ሕይወት እንድናጣ ያደረጉንን መታገል መብት እንጂ ወንጀል አይደለምና አንፍራ !*

- *ከመጀመሪያው ክብ የመጨረሻዎቹ ቀለበቶች ሲበጠሱ፤ የጭቆናው ሰንሰለት ይበጠሳል፤ የጭጋግ ዘመን አልፎ የተሰፋ ብርሃን ይፈነጥቃል !*

- *አገር በምርቃት አይቀናም፤ ጠላትም በእርግማን አይጠፋም፤ ትግል በውክልና ፡ ድልን መልመና ፡ መቋመጡን ትተን በአንድነት ለመታገል እንነሳ !*

- *ኢትዮጵያ ቀደም ብላ ተፈጥራለች የቀረን እራሳችንን መፍጠር ነው፤ እያንዳንዱ ሰው እራሱን ለመፍጠር የሚያስብ አይምሮና የሚሠሩ እጆች ያብቅል !*

- *ደርግም ሆነ ወያኔ ከአንድ ዛፍ የተመለመሉ ቅጠሎች ናቸው፤ የምርጥ መኮንኖች አብዮት፤ በምርጥ ሌቦች አብዮት ሲተካ፤ አገር ተሸጠ፤ ውሸት ነገሠ፤ታሪክ ተፋቀ፤ ዜጋ ተፈናቀለ፤፤ ባዕድ ጠገበ፤ ዜጋ ተራበ ።*

***ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!***
***ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !!***

*ጥር 14 ቀን 2004 ዓ.ም (2012- 01-23)*